**ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH**
**IN DALLAS**
**9150 GARLAND ROAD**
**DALLAS, TX 75218**

ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH
DALLAS, TX 75218





መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣
ሩጫውን ጨርሼአለሁ፣
ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፣
ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣
ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለ ያሰረክበል፣
ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእ ቻ አይደለም።"
2ጢሞ. –8

# አገልግሎትና

# የጽድቅ አክሊል

ከ ዶ ክ ተ ር ዓ ለ ሙ ቢ ፍ ቱ

፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ታተመ።
(1992 እ. አ. አ.)



ይህ መጽሐፍ ቀደም ሲል "አገልግሎትና የጽድቅ አክሊል ለመንፈሳዊ መሪ" በሚል ስያሜ በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ለመጀመሪያ ታትሞ ወጥቶ ነበር። ይህ ሁለተኛ እትም "አገልግሎትና የጽድቅ አክሊል" በሚል ርእስ ተሻሽሎና ዳብሮ ከአምስት ተጨማሪ ምዕራፎች ጋር ቀርባል።

ይህንን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት ወይም ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።
© Copyright Alemu Beeftu, May, 1992.
All rights reserved
PRINTED IN THE U.S.A

ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH
9150 GARLAND RD.
DALLAS, TX 75218

# ማውጫ


| ምዕራፍ | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | 8 |
| መግቢያ | |
| ምዕራፍ-1 ከመሪነት አገልግሎት በፊት የሚቀድም ጥሪ | 15 |
| ▶መሪ ማለት ምን ማለት ነዉ? | 18 |
| ▶የአገልግሎት ምንነት | 19 |
| ምዕራፍ-2 የመንፈሳዊ መሪ ጥሪ | 27 |
| ▶የአገልግሎት ጥሪና የክርስቶስ ምሳሌነት | 28 |
| ምዕራፍ-3 መሪዎች የሚጠሩት በማን ነው? | 39 |
| ▶በእግዚአብሔር በተጠሩትና ባልተጠሩት መሐከል ያለው ልዩነት | 42 |
| ምዕራፍ-4 የአገልግሎት ዝግጅት | 49 |
| ▶ለአገልግሎት መዘጋጀት | 51 |
| ምዕራፍ-5 ለአገልግሎት ማዘጋጀት | 65 |
| ምዕራፍ-6 የመንፈስ ቅዱስ ቅባትና የአገልግሎት ሕይወት | 72 |
| ▶እግዚአብሔርን የሚያስከብር አገልግሎት | 72 |
| ▶የአገልግሎት ቅባት በብሉይ ኪዳን | 76 |
| ▶የክርስቶስ የአገልግሎት ቅባት | 80 |
| ምዕራፍ-7 ለአገልግሎትና ለአገልጋዩ የሚሰጥ ቅባት | 86 |
| ▶የመንፈስ ቅዱስ ቅባት አስፈላጊነት | 90 |
| ▶የመንፈስ ቅዱስን ቅባት መቀበል | 94 |
| ▶የመንፈስ ቅዱስን ቅባት መጠበቅ | 98 |
| ምዕራፍ-8 ጥቂት ጊዜ | 103 |
| ምዕራፍ-9 መሪዎች ለምን ይጠራሉ? | 113 |
| ▶ለጽድቅ ሥራ ምሳሌነት | 114 |
| ▶በመከራ ዘመን ተስፋ እንዲሆኑ | 115 |
| ▶ሕዝቡን ከባርነት እንዲያድኑ | 117 |
| ▶ቤቱን እንዲሠሩ | 119 |
| ▶ሕዝቡን በረከት እንዲያወርሱ | 121 |
| ▶የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲጠብቁ | 122 |
| ▶መላከታዊ ምስጢር እንዲገልጡ | 123 |
| ምዕራፍ-10 የአገልግሎት ራእይ | 125 |
| ▶የሚጠራውን ጌታ ማየት | 127 |
| ▶ተገልጋዩን ማየት | 130 |
| ▶የመከሩን ጌታ ማየት | 132 |
| ▶የሚያገለግለውን ጌታ በክብሩ ማየት | 132 |
| ምዕራፍ-11 ከመሪ የሚጠበቁ ነገሮች | 136 |
| ▶መጋለጥና ማስተዋል | 136 |
| ▶ሰባት ዓይነቶቹ መሪዎች | 137 |
| ▶ትሑት ልብ | 144 |
| ▶የአገልግሎት መንፈስ | 145 |
| ▶አስተዋይ አእምሮ | 146 |
| ▶ሙያና ችሎታ | 147 |
| ምዕራፍ-12 ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ መሪዎች | 149 |
| ▶ሐዋርያት | 149 |
| ▶ነቢያት | 151 |
| ▶ወንጌላውያን | 153 |
| ▶እረኞች | 154 |
| ▶መምህራን | 155 |
| ▶ኤጲስ ቆጶስ | 155 |
| ▶ሽማግሌዎች | 155 |
| ▶ዲያቆናት | 156 |

▶የጥሪዎችና የአገልግሎቶች መሠረት 159
▶የአመራርና የአስተዳደር አገልግሎት 160
▶የመሪነትና የአስተዳዳሪነት ዝንባሌ 161
ምዕራፍ–13 ከመሪና አስተዳዳሪ የሚጠበቁ ችሎታዎች 166
▶ራእይና እርቆ ማየት 166
▶የአስተዳደር ችሎታ 168
▶የመምራት ችሎታ 170
▶የመለየት ችሎታ 171
▶የማቀነባበር ችሎታ 172
▶ሃላፊነት የመስጠት ችሎታ 172
▶ሌሎችን የማዘጋጀት ችሎታ 174
▶ውሳኔ የማድረግ ችሎታ 175
▶የቻይነትና የልበ ሰፊነት ችሎታ 178
▶በእምነት የመኖር ችሎታ 179
ምዕራፍ–14 መሪ በአመራርና በአስተዳደር አገልግሎት ላይ 182
▶መሪ ሥራውን ከየት ይጀምራል? 182
▶መሪ ሥራውን እንዴት መጀመር ይኖርበታል? 184
ምዕራፍ–15 መሪን በአገልግሎት ላይ የሚገጥሙት ፈተናዎች 198
▶ከውስጥ የሚነሱ ፈተናዎች 198
▶ከሰይጣን የሚመጡ ፈተናዎች 205
▶ከሁኔታ የሚመጡ ፈተናዎች 208
ምዕራፍ–16 የመሪ ሕይወት–ክፍል አንድ 217
▶መሪ ሕይወቱን እንዴት ይጠብቃል? 217
ምዕራፍ–17 የመሪ ሕይወት–ክፍል ሁለት 232
▶መሪ ሕይወቱን ከምን ይጠብቃል? 232
▶ከገንዘብ ፍቅር 233
▶ጤናማ ካልሆነ የጾታ መቀራረብ 235
▶ትክክል ካልሆነ የሥልጣን አጠቃቀም 236
▶ለዝናና ለተወዳጅነት ከማገልገል 237
ምዕራፍ–18 መደምደምያና አጠቃላይ ሃሳብ 240
▶ጌታ ለመሪዎች የሚያስተላልፉቸው ጥሪዎች 244
▶ኑና እዩ 244
▶ኑና ተከተሉኝ 245
▶ኑና ዕረፉ 246
▶ኑና ብሉ 247
▶ኑና ውረሱ 248
▶ዋቢ መጻሕፍት 250

## መቅድም

በዘመናት ሁሉ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መልእክት ነበረው። ለቤተ ክርስቲያንም መልእክት ነበረው። ይህንን መልእክት ወዶና መርጦ በሰዎች በኩል ማስተላለፍ ፈለገ። መልእክቱን የሚያስተለልፉትን ሰዎች በመሪነት አገልግሎት ላይ እንዲቀመጡ ለያቸው። በእግዚአብሔር ፊት መሪ መሆን አገልጋይ መሆን ነው። አሽከር መሆን ማለት ነው። ስለዚህም፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሪና አገልግሎት ተቀራርበው ተተንትነዋል። የመሪ ጥሪና የአገልግሎት መንፈስ በሰፊው ተብራርቷል። እንዲህ ዓይነቱ መጽሐፍ ለአገራችን ቤተ ክርስቲያን አዲስና የመጀመሪያ ከመሆኑም በላይ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ አገልጋዩን አሳስቦ መመሪያውን ላቀረበልን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን። አገልጋዩንም አብዝቶ ይባርከው።

መሪ ሲባረክ ቤተ ክርስቲያንም ትባረካለች። መሪ በራእይ ሲያድግ ቤተ ክርስቲያንም በራእይ ታድጋለች። በአንጻሩም ደግሞ፣ መሪ ሲደክምና አስተሳሰቡም ጠባብ ሲሆን የቤተ ክርስቲያንም አመለካከት እንዲሁ ጠባብና ደካማ ይሆናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፤ በአዕምሮ መብሰል፣ ልበ ሰፊ መሆን፣ ጥሪን ልይቶ ማወቅ፣ ለአገልግሎት መዘጋጀትና ሌሎችም መሪንና ቤተ ክርስቲያንን የሚገነቡ ሃሳቦች በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ተተንትነዋል። የደራሲው ምኞት፣ የቀረቡት ሃሳቦች በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ መመሪያዎች መሆናቸውንና፣ በሥራ ላይ ብናውላቸው አገልግሎታችን የበለጠ ፍሬያማ እንደሚሆን ለማሳየት ነው። በሌላው በኩል ደግሞ፣ የመጽሐፉ ዓላማ፣ መሪን ወይም አገልጋይን አስመልክቶ ለሚመጣው ጥያቄ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሳይሆን፣ የሚያወያይ ወይም መንደርደሪያ የሚሆን ሃሳብ ለመስጠት ነው። መጽሐፉን በዚህ መንፈስ ብናነበው ብዙ ይጠቅመናል።

ደራሲው እንደጠቀሰው በዘመናችን ለእግዚአብሔር የተለዩ፣ ቆራጥና የሐዋርያት ቅባት ያላቸው አገልጋዮች ያስፈልጉናል። ጥንት፣ ክርስትና ገና ስትወለድ፣ ለእሥር ቤት ስንሰለት፣ ለሰይፍ እፎት፣ ለአንበሳ እፍ ነው የተጣለችው። ይሁን እንጂ፣ ቆራጥ አገልጋዮቿ በሕይወታቸው ሕይወትን ሰጧት። በደማቸው፣ አሁን እያጨድን ያለውን የወንጌል አዝመራ ዘር ዘርተውልን አለፉ። ጠረጤሊያኖስ እንዳለው፣ "የሰማእታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር" ሆነ።

አዎን፤ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ለመወጣት ብዙ መስዋእትነት ከፍላለች። በአንድ በኩል፣ "ከእኛ ልምምድ ሌላ ሃይማኖትለዘበት" የሚለው የአይሁዳውያን ባህላዊ ኃይማኖት አጥር፤ በሌላ በኩል፣ ለሥጋ ደስታና እርካታ ብቻ የቆመው የግሪኮች ምድራዊ ፍልስፍና፤ እንዲሁም ደግሞ በዚያን ጊዜ በዓለም የተንሠራራውና እቻ ያልነበረው የሮማውያን መንግሥት፣ የሰውን አዕምሮ ወጥሮ በያዘበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ድምጿን ከማሰማትና መልእክቷን ለማስተላለፍ ያደረገችው ሙከራ ቀላል አልነበረም። በዚያን ጊዜ በነበረው ሕብረተሰብ ውስጥ የማያጠራጥርና የማያሻማ፣ ዘመናትን እልፎ ለእኛም ምሳሌ የሆነን ለውጥ አድርጋ አልፋለች። ለውጥ ያመጣው ቆራጥ የሆኑት የአገልጋዮቿ ምስክርነትና በደሙ ኃይል የተቀዳጁት ድል ነበር። (ራእ. 12:11) በአጭር ጊዜ ውስጥ:- ምድራዊ እውቀትና ብዙ ሃብት ንብረት ያልነበራቸው ሰዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ያልታወቁና የተናቁ ሰዎች በወንጌል ኃይል ምድርን ገለባብጠዋት አለፉ።

ዛሬም ሰማያዊውን ኃይል በካደና የአምልኮት መንፈስ በበዛበት ዓለም ውስጥ እንኖራለን። ሁሉን ነገር ለገል ምቾትና ደስታ እየተባለ በሚፎከርበት ዘመን እንመላለሳለን። እንደያኔው ቤተ ክርስቲያን ዛሬም በሕብረተሰብ ውስጥ ዘለቄታ ያለው ለውጥ ለማምጣት ትችላለች። ይህ እንዲሆን ግን:- በእግዚአብሔር የተጠሩና ለእርሱ የተለዩ አገልጋዮች እርሱ ለሚሰጠው ዘላለማዊ ተስፋ ቆርጠው የተነሱ መሪዎች ያስፈልጋሉ። የድሮዎቹ አገልጋዮች ወርቅና ብር አልነበራቸውም የእግዚአብሔር ክብር

ግን በሙላት ነበረባቸው። ምድራዊ ኃይል ወይም ሠራዊት አልነበራቸውም። በሰማያዊ ኃይል ግን ተሞልተው ነበር። ስለሆነም በእምነት በመኖርና በመሥራት ጌታን አስከብረው አለፉ። (ዕብ. 11:33–35)

እነዚህ አገልጋዮች በሰማያዊ ኃይል ስለተሞሉ የትንሣኤን ኃይል ሰበኩ፣ በኢየሱስ ስም በሽተኞችን ፈወሱ፣ አጋንንትን አስወጡ። የእግዚአብሔር ቅባት በሕይወታቸው በሙላት ከመፍሰሱ የተነሳ ጥላቸው እንኳን በሽተኞችን ይፈውስ ነበር። የልብሳቸውም ቁራጭ ድንቅና ተአምራት ይሠራ ነበር። በነፃ የተቀበሉትን በነፃ ሰጡ። ቤተ ክርስቲያን ከምንጊዜም የበለጠ ዛሬ ወደዚህ ልምምድ የሚወስዱአትና የሚያደርሱአት መሪዎችና አገልጋዮች ያስፈልጓታል። እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉትን አገልጋዮች እየቀባ እንዲያስነሳልን እንፀልይ።

ይህ ዓይነቱ ጥሪና አገልግሎት የከበረ ነው። መላእክት የሚቀኑለት አገልግሎት ነው። የገሃነም ደጆች የማይቋቋሙት አገልግሎት ነው። ሐዘንን በደስታ፣ በሽታን በፈውስና ሞትን በሕይወት የሚሽር አገልግሎት ነው። የተጠሩት አገልጋዮች ወደዚህ ዓይነት ልምምድ የሚደርሱት ከእግዚአብሔር ጋር ብቻቸውን ጊዜ በማሳለፍ ነው።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲጠግብ፣ አምላኩም በመካከሉ ሲመላለስና ሲሠራ እንዲያይ የመሪዎች ልብና መንፈስ መዘጋጀት በጣም አስፈላጊ እርምጃ ነው። ይህ መጽሐፍ የተጻፈውም ይህንን ዝግጅት የሚያፋጥኑ አቢይ ሃሳቦችን ለመጠቆም ነው። መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ሰምተን በሥራ ላይ እንድናውለው እግዚአብሔር ይርዳን።

ከዶክተር ቤተ መንግሥቱ



## መግቢያ

### ስለመጽሐፉ አጠቃላይ ሃሳብ

ክርስቶስ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን ሊኖረው የሚገባው ቦታ ማስተዋል በነፃነት በመኖርና በመሥራት ፍሬያማ አገልግሎት እንድናበረክት ያስችለናል። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የመንፈሳዊ መሪ ሕይወት፣ ጥሪ፣ ስጦታና አገልግሎት ራስና መሠረት ጌታ ኢየሱስ መሆኑን በማሳየት – በአገልግሎት ላይ ያሉ ሥራቸውን ለመገምገም እንዲችሉና ለአገልግሎት ለሚዘጋጁት ደግሞ መመሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ሃሳቦች ለመስጠት ነው።

መጽሐፉ ክፍሬያማ አገልግሎት የተጠራ መሪ ከአገልግሎት በፊት ማስቀደም ስለሚገባቸው ነገሮች ከማብራራቱም በላይ "መሪ ማለት ምን ማለት ነው?" የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ይመልሳል። የክርስቶስን ምሳሌነት በመጠቀም የአገልግሎትን ጥሪና የአገልጋይን ኃላፊነት ያብራራል። በእግዚአብሔር የተጠሩ መሪዎችን ከሌሎች ለይቶ አይነተኛ የሚያደርጋቸው ነገሮችና የአገልግሎታቸዉን ራእይ በሰፊው ያብራራል። ከመንፈሳዊ መሪ የሚጠበቁ ችሎታዎችን ከመተንተኑም በላይ ሰባት ዓይነት መሪዎች እንዳሉና የራእያቸውን ልዩነት በቃላት ብቻ ባይሆን በሥዕል እየተጠቀመ ያስረዳል። ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡትን መሪዎች (ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣ አስተማሪዎች፣ እረኞች፣ ሽማግሌዎችና የመሳሰሉትን) ከመግለጹም በላይ የመሪንና የአስተዳዳሪን ልዩነትና ዝንባሌ ይተነትናል።

ከዚህ ጋር ለአመራርና ለአስተዳደር የተጠሩት መሪዎች አገልግሎታቸውን ለመፈጸም የሚያስፈልጉትን ችሎታዎች ምን ምን እንደሆኑ ይገልጻል። አገልጋይ የአመራርና የአስተዳደር አገልግሎቱን ከመጀመሪያ

ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድረስ እንዴት በቅደም ተከተል ማካሄድ እንዳለበት የነሀምያን ምሳሌ በመጠቀም ያብራራል። መሪ በአገልግሎት ላይ ከተሰማራም በኋላ ሊያገጥሙት የሚችሉትን ፈተናዎች ምን እንደ ሆኑና መነሾዎቻቸውንና የማሸነፊያ መንገዶችን ይጠቁማል። በተጨማሪም የጌታ አገልጋይ ሕይወቱን እንዴትና ከምን መጠበቅ እንደሚገባው መመሪያ የሚሆኑ ሃሳቦችን ይሰጣል። በመጨረሻም ክርስቶስ  በመሪ አገልግሎት ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ቦታ አሳይቶ፣ ጌታ ኢየሱስ መሪዎችን "ኑ" በማለት የሚጠራቸው ለአገልግሎት ብቻ ሳይሆን ጥሪው ለአክሊልም መሆኑን በማስረዳት የመጽሐፉን ሃሳብ ይደመድማል።



## ማሳሰቢያ

ሌላው ለአንባቢ ላሳስብ የምፈልገው ስለመንፈሳዊ መሪ ሁሉንም ነገር በአንድ መጽሐፍ ለማስፈር መሞከር አስቸጋሪ ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጠቀስኳቸው፣ ፅንስ ሃሳቦች ለመስጠት ያህል እንጂ ስለ መሪ ሁሉንም ነገር ለመጻፍ ያለ መሆኑን ነው። እንዲሁም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈሩትን ሃሣቦች አንባቢ የጌታን ቃል በይበልጥ እያነበበ እንዲመረምር ለማበረታታት ነው። ሃሳቤን ለማስፋት ካነበብኳቸው መጻሕፍት ጥቂቶቹን በመጨረሻ ላይ ዘርዝሬአቸዋለሁ።

ገና ብዙ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች ስላሉና ስለዚህም የግድ ከአንድ ቦታ መጀመር አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት ይህችን መጽሐፍ በብዙ ፀሎት ለአንባቢ በረከት ለጌታም ክብር ትሆናለች ብዬ አቅርቤአለሁ። የአንድን ብላቴና ምሳ ወስዶ ከአምስት ሺህ በላይ የሆኑትን መመገብ የሚችል ጌታ ኢየሱስ ታማኝ ስለሆነ ደስ እያለኝ እነሆ አምስቱን ዳቦዉንና ሁለቱን ዓሣዎች በእጁ አኑሬአለሁ። ጌታ ለበረከት እንዲያደርግልዎት ጸሎቴ ነው።

## ምሥጋና

ከሁሉም በፊት በአገልግሎቱ ውስጥ ተካፋይ እንድሆን ዕድል ለሰጠኝና የተሰጠኝንም በረከት ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳቀርብ በፀጋና በፍቅሩ ዕድል የሰጠኝን ታላቁን አምላኬን ከልቤ አመሰግነዋለሁ፤ ክብርንም ሁሉ ለስሙ እሰጣለሁ።

ይህችንም መጽሐፍ ሆነ ወደፊትም በመጻፍ ላይ ያሉትን መጻሕፍት ለመጻፍ የጀርባ አጥንት በመሆን ረዳቴም ጸሐፊዬም ሆና ለጌታ ክብር አብራኝ ስለቆመች ስለ ባለቤቴ ወይዘሮ ገነት ያዕቆብ ጌታን ከልቤ አከብረዋለሁ። እርስዋንም ጌታ ይባርክሽ ልላት እወዳለሁ። እህቴ ሠናይት ያዕቆብ ታይፕ በማድረግ ስለሰጠችው አገልግሎት ሁሉ በጣም አድርጌ አመስግናታለሁ። የመጀመሪያውን ረቂቅ አንብበው ጠቃሚ ሀሳብ በመስጠት ለጌታ ሥራ ያበረታቱኝን ወገኖቼን ሁሉ በተለይም ወይዘሪት ጥሩወርቅ መስፍንን፣ አቶ ጌታቸው ጩኮን፣ አቶ መንግሥቱ ለማን፣ አቶ ብርሃኑ ምትኩን፣ አቶ ብርሃነመስቀል ደጀኔን፣ አቶ ድንቁ ጃለታን፣ ዶክተር ቤተ መንግሥቱን፣ ዶክተር ቶሎሳ ጉዲናንና አቶ በፈቃዱ ኃይሌን ጌታ ይባርካችሁ እያልኩ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ። ጌታ እንደዚህ ካሉት ባሪያዎች ጋር እርሱን ለማገልገል እድል ስለሰጠኝ በጣም ደስ ይለኛል።

ዶ/ር አበራ ሞላም ይህን መጽሐፍ ያለ ብዙ ችግር ለማሳተም እንድችል የአማርኛን ኮምፒውተር መጻፊያን ፕሮግራም በማዘጋጀት ለዚህ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን ለሕዝባችን ስላበረከተው አስተዋጽዖ በአንባቢዎቼ ስም ላመሰግነው እወዳለሁ።



## ም ዕ ራ ፍ  አ ን ድ

### ከመሪነት አገልግሎት በፊት የሚቀድም ጥሪ

"ለዘላለም ለእኔ እንድትሆኚ እጭሻለሁ፤ በጽድቅና በፍርድ በምህረትና በርህራሄ እጭሻለሁ። ለእኔም እንድትሆኚ በመታመን እጭሻለሁ፤ አንቺም እግዚአብሔርን ታውቂያለሽ።" (ሆሴ. 2:21–22)

ለአዳም ልጆች የተላለፈው የእግዚአብሔር ጥሪ ለሕይወትና ለአንድነት ነው። እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ሕዝቡን ሲጠራ ለእርሱ እንዲለዩለትና ለእርሱ ብቻ እንዲሆኑ ነው። ታማኝ ሴት ለባልዋ ብቻ ተለይታ ራሷን በንጽህና በመጠበቅ ከባልዋ ጋር ያላትን አንድነት በትጋት እንደምታጠነክር ሁሉ፣ የእግዚአብሔርም ዋነኛው ጥሪ ለእርሱ በመለየት በፍጹም ሕብረት ከእርሱ ጋር እንድንኖር ነው። በሌላ አነጋገር ሰውን ለራሱ ሲለይ ራሱን ሊገልጥለት፣ ምሕረቱን ሊያሳየው፣ ፍቅሩን ሊያለማምደው፣ በቅድስና ሊያኖረውና ሕይወቱን ባርኮ ለሌሎች በረከት ሊያደርገው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። <u>ከሁሉም ልምምድ የሚቀድመው እርሱን ማወቅ ነው</u>። ይህ ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ "አንችም እግዚአብሔርን ታውቂያለሽ" የሚል ሐረግ ይደጋገማል። የሕይወት መሠረትና ከጥሪ ሁሉ ቀዳሚው እግዚአብሔርን ማወቅና ምህረቱን ተቀብሎ በፀጋው የእርሱ መሆን ነው።

እንግዲህ አገልግሎት የሚጀመረው ድርጊቶችን በመፈጸም ሳይሆን የሚከተሉትን አምስት ዓቢይ ነገሮች በመለማመድ ነው።

## 1ኛ› ምህረቱን ተቀብሎ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በመመሥረት ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው:- "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና"። (ዘፍ. 5:24) እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ የሚጠራው አካሄዳችንን ከእርሱ ጋር እንድናደርግ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለዚህ ጉዳይ ሲያብራራ እንዲህ ይላል:- "ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።" (1ኛ ዮሐ. 1:3)

## 2ኛ› የእግዚአብሔር ወዳጅ በመሆን።

የእግዚአብሔር ቀዳሚ ጥሪ ለወዳጅነት ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን በጠራው ጊዜ "ተለይተህ ወደማሳይህ አገር ሂድ" አለው። አብርሃምም በእምነት ታዝዞ ለእግዚአብሔር ከተለየ በኋላ እንደ ጻደቀ፣ ደግሞም ተባርኮ ለምድር ሕዝብ ሁሉ በረከት እንደ ሆነና የእግዚአብሔርም ወዳጅ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርለታል። "...አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።" (ያዕ. 2:23)

በአዲስ ኪዳን ግን ወዳጅ መሆን ከልጅነት ጋር የተጣመረ የፀጋ ስጦታ መብት ነው። ይህ ልጅነት የሩቅ ወዳጅነት ሳይሆን የራሱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆን ነው። "አባ፤ አባት" ብሎ በመንፈስ ቅዱስ እማኅኝነት እግዚአብሔርን ለመጥራት መቻል ነው። ሁሉንም የሚችል፣ ሁሉንም የሚያውቅ፣ በሁሉም ቦታ የሚገኝና፣ የማይለወጠው የቅዱስ እግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው። ይህም ማለት በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ክብር ብቻ ሳይሆን ከመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆንን ያጠቃልላል ማለት ነው። "ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።" (2ኛ ጴጥ. 1:4)



## 3ኛ› እግዚአብሔርን በመምሰል።

እግዚአብሔርን መምሰል ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ አይደለም። ስለ እግዚአብሔር መዘመርም አይደለም። እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ አውቆ እርሱን ወደ መምሰል መለወጥ ነው። ይኸውም የእግዚአብሔርን ቅድስና ማወቅ፣ ታላቅነቱን ማወቅ፣ ገናናነቱን ማወቅ፣ አዳኝነቱን ማወቅ፣ ፍቅሩን ማወቅ፣ ምሕረቱን ማወቅ፣ ማንነቱን ማወቅና ክብሩንም ሁሉ ማየት ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስንመለከት የእግዚአብሔር ጥሪ እርሱን እንዲያውቁትና፣ ካወቁትም በኋላ በሕይወታቸው ውስጥ እንዲያከብሩትና እንደ አምላክነቱም መጠን እንዲፈሩት ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ ስናይ ጥሪው ከዚያ የጠለቀ ነው። ከማወቅም አልፎ እርሱን ወደ መምሰል እንድንለወጥ ነው። "ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፣ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናአልና ፤" (ሮሜ. 8:29)

## 4ኛ› እግዚአብሔርን በማምለክ።

እውነተኛ ኅብረት፣ ወዳጅነትና እውቀት ግብዝነት ወደ ሌለበት አምልኮ ይመራል። እግዚአብሔር ሰውን የጠራውና ለራሱ የለየው፣ ስለሚያደርግላቸው እንዲያመሰግኑት ወይም በለሚያስፈልጋቸው ነገሮች እንዲለምኑት ብቻ አይደለም። ታላቁ ዓላማውና ፍላጎቱ ግን በሙሉ ልባቸው፣ በሙሉ ነፍሳቸው ፣ በሙሉ ኃይላቸውና ከዚያም አልፎ ባላቸው ሁሉ እንዲወዱት፤ ይህንንም ፍቅር በአምልኮ እንዲገልጹለት ነው። አምልኮ:- እግዚአብሔርን መውደድና ስለማንነቱ እርሱን ማወደስ፣ በጉልበት ብቻ ሳይሆን በሀሳብም በእርሱ ፊት መንበርከክ ነው። የአዲስ ኪዳን ጥሪም ሰዎች እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ እንዲያመልኩት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራው ለዚህ ነው። ከዚህ የሚበልጥ አገልግሎት የለም። እውነተኛ አምልኮ አገልግሎት ነው። እውነተኛ አገልግሎትም አምልኮ ነው።

## 5ኛ እግዚአብሔርን በመታዘዝ።

“ኖህም እንዲህ አደረገ፤ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ።” (ዘፍ. 6:22፣ 7:5) መታዘዝ የእግዚአብሔር ሰዎች ምልክት ነው። አብርሃም ታዘዘ፣ ሙሴ ታዘዘ፣ ኢያሱ ታዘዘ፣ ነቢያት ታዘዙ፣ እንዲሁም ሐዋርያት “ ... ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ልንታዘዝ ይገባል፣” አሉ። (የሐዋ.5:29) የጌታ ቃል ስለ ክርስቶስ “ለሞት ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ።” ይላል። (ፊል. 2:8)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ከመሪ ጥሪና ከአገልግሎት ሃላፊነት የሚቀድሙ ብቻ ሳይሆኑ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ቀዳሚ ጥሪዎች እግዚአብሔርን ለመከተል ለወሰኑ ሁሉ የተሰጡ አገልግሎቶች ናቸው። ይኸውም ስጦታን የሚመለከቱ ነገሮች ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ሕያዋን የመሆናችን ማረጋገጫዎች ናቸው። እነዚህን በሕይወቱ የማይለማመድ ማንኛውም ክርስቲያን ስጦታ አለኝና ላገልግል ቢል አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ፊት መታሰቢያነት የለውም። ሕይወት የአገልግሎት ፍሬ አይደለም። እግዚአብሔር የሚቀበለው አገልግሎት ግን የሕይወት ፍሬ የመሆን ውጤት ነው።

### መሪ ማለት ምን ማለት ነው?

መንፈሳዊ መሪ ማለት የተሰጠውን መንፈሳዊ አገልግሎት ወይም ሥራ ለማከናወን በአገልግሎት ሌሎችን በመቅደም ምሳሌ የሚሆን ሰው ማለት ነው። መሪ ሌሎችን የሚቀድመው በጉልበት ሥራ ብቻ ሳይሆን እቅድ በማውጣት፣ ግብ በመተለም፣ የአሠራር ዘዴን በማሳየት፣ መንገድ በመቀየስና ሁኔታዎችን ለአንድ የታወቀ ዓለማ በማመቻቸት ነው። እንግዲህ መሪ አገልጋይ፣ ሠራተኛና ከዚያም አልፎ የክርስቶስና የተከታዮቹ ሎሌ ነው። መሪን ልዩ የሚያደርገው አገልጋይነቱ፣ ሠራተኛነቱና ሎሌነቱ ነው።



ይህንንም የሚገልጸው በአመራርና በአስተዳደር ሥራ ላይ ሆኖ ነው። መሪም የምንለው ለዚህ ነው። በዚህ ውስጥም ትልቁ ኃላፊነቱ የሚመራቸውን ሰዎች መድረስ ወደሚገባቸው ግብ ማድረስና፣ መሆን የሚገባቸውን እንዲሆኑ ወደ ከፍተኛ ቦታ መምራቱ ላይ ነው። የአመራር ጉዞ የመኅልመስና የእድገት ጉዞ ነው። በትክክለኛ ሥራና አሠራር ውስጥ መሪውና ሕዝቡ አብረው በእውቀት፣ በጥበብ፣ በአእምሮ፣ በመንፈስ፣ በስሜትና በችሎታ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያድጋሉ። እድገት በተፈጥሮ የተሰጠ ነገር ቢሆንም ይህ ዓይነቱ እድገት በሥጋ ከማደግ የሚለይበት አንዱ መንገድ ፈቃደኝነትን ስለሚጠይቅ ነው። ስለዚህ መሪውም ሆነ ሕዝቡ አብሮ ለማደግ ፈቃደኞች መሆን ይኖርባቸዋል።

### የአገልግሎት ምንነት

ስለ መንፈሳዊ መሪ ከመተንተኔ በፊት በአጭሩ ስለ አገልግሎት መሠረታዊ የሆነውን ነገር ማብራራት አስፈላጊ ይመስለኛል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ለሰዎች ብዙ ስጦታዎችን ይሰጣል። (በተለይም ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በ1ቆሮ. 12፣ 13፣ 14፣ በኤፌ 4 ና በሮሜ 12 ተዘርዝሮልናል።) እነዚህን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚያስተምሩንን ምዕራፎች በአጠቃላይ ከብሉይ ኪዳን ምዕራፎች ጋር ስናስተያይ በጣም ጥቂቶች ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህም ማለት ደግሞ ስጦታዎች (በጣም) አስፈላጊዎች አይደሉም ለማለት ሳይሆን፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያንም የተሰጡ ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያንም በዓለም እስካለች ድረስ እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ በውስጧ ይሠራሉ ለማለት ነው። የተሰጡበትም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን እድገትና እንዲሁም በነፍስ ወከፍ ለእያንዳንዱ አማኝ መታነጽ እንዲሆን ነው።

የእያንዳንዱ አማኝ በነፍስ ወከፍ መታነጽ ግን ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር የስጦታ እጥረት የለውም። ካስፈለገ ከአሁን በፊት ያልታየውን ስጦታ መስጠት የሚችል አምላክ ነው። ነገር ግን

የእግዚአብሔር ጉዳይ ከልብና ከሕይወት ጋር ነው። የመንፈሳዊ ሕይወት ፍሬ የጐደለው አገልግሎት እንዲያው ስጦታን ማሳያ ነው እንጂ፣ ቅን መንፈሳዊ አገልግሎት አይደለም። የቀሩት የአዲስ ኪዳን ምዕራፎች ሁሉ ስለ ክርስትና ሕይወት መመሪያ ለመስጠት የተጻፉት ለዚህ ነው ። የአገልግሎት መሠረት በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ነጽቶ፣ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል ተቀድሶና ተሞልቶ ጤናማውን የክርስትና ሕይወት መኖር ነው። ጤናማው የክርስትና ሕይወት ደግሞ በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ በተለይም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምናነበው ነው። ይህ ስለሆነ ማንኛውም ዓይነት አገልግሎት ቢሆን ለመንፈሳዊነት ወይም ለታይታ የሚለበስ ካባ ሳይሆን በቃሉ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ የሚገልጸው ፍሬ መሆን አለበት። የአገልግሎትን ፍሬ ለማፍራት በክርስቶስ ውስጥ መሆን፣ በመንፈሱና በቃሉ መሞላት፣ እንዲሁም በፍቅሩ መመላለስ ያስፈልጋል። "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል። ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል።" (ዮሐ. 15:7-8) አብን የሚያስከብረው አገልግሎት፣ እንደ አሁድ ልብስ የሚለበስ ሥራ ሳይሆን ከውስጥ የሚወጣ የሕይወት ፍሬ ነው። ይህም ማለት መንፈሳውያን ለመሆን እናገለግልም፤ ነገር ግን መንፈሳውያን ስለሆንን በተሰጡን የተለያዩ ስጦታዎች አማካይነት የሕይወትን ፍሬዎች እያፈራን እግዚአብሔርን እናገለግላለን።

የተጠራነው ለልጅነት ስለሆነ እንደ ልጆቹ ከኖርን የመታዘዝን ጠባይ እናሳያለን። ይህም ሲሆን ለልጅነት የጠራን አምላክ ታማኝ አድርጎ ስለሚቆጥረን የሥራን ወይም የአገልግሎት ድርሻን ይሰጠናል። ትኩረቱ ደግሞ ከስጦታው ወይም ከአገልግሎቱ ዓይነት ላይ ሳይሆን የእኛ ታማኝ ሆኖ ማገልገሉ ላይ ነው። ደግመን እናስተውል:- አገልግሎት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ታማኝነትም ነው። ታማኝነት ደግሞ የውጫዊ ነገር ሳይሆን የልብ ጉዳይ ነው። እንግዲህ የእግዚአብሔር ጉዳይ ከልባችን ጋር ነው። የሕይወት መውጫ ከልባችን ነውና፣ "አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።" ይላል። (ምሳ. 4:23)

በአገልግሎት ውስጥ ታማኝነት አስፈላጊ ነገር ከሆነ፣ ታማኝ



ለመሆን ደግሞ አደራውን የሰጠን ማን እንደሆነና አደራውም ምን እንደ ሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ፍሬያማ አገልግሎትን ለማበርከትና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ራሱን ለጌታ የሚለይ ሁሉ ከአገልግሎት ጥሪው አስቀድሞ የሚከተሉትን አምስት ፍሬ ነገሮች መረዳት አለበት።

## ፩ኛ የጠራውን ጌታ ማወቅ።

ቀደም ብዬ እንደ ጠቀስኩት ከሁሉም የሚቀድመው ጥሪ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። አገልጋይ በተለይም የአምላኩን ማንነት መረዳትና በስሙም እንዲያውቀው ያስፈልገዋል። በተፈጥሮ ጠባዩንና ማንነቱን የማንረዳውን ሰው እንኳ ማገልገል በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ አገልጋይ የአምላኩን ማንነት በጥንቃቄ ማጥናት ይገባዋል። ማለትም ስለ እግዚአብሔር:- ቅድስና፣ ችሎታ፣ ኃይል፣ ግርማ፣ ታላቅነት፣ ፈጣሪነት፣ አዳኝነት፣ አባትነት፣ አፍቃሪነት፣ መሐሪነት፣ ፈራጅነት፣ ወዘተ በጥልቀቱ መረዳት ያስፈልጋል። አገልጋይ እነዚህን ሲረዳ ሕይወቱ ምልዓት ይኖረዋል፤ አገልግሎቱም ፍሬያማና የተባረከ ይሆናል። እንግዲህ ከአገልግሎት በፊት የሚቀድመው ጥሪ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መረዳትና በኑሮም በአገልግሎትም ሁሉ ሥልጣንን ለእርሱ መስጠት ነው። ይህ ከሆነ የአገልግሎቱ ፍሬ ዘለቄታ ያለው ይሆናል።

## 2ኛ በእግዚአብሔር ውስጥ ማንነቱን ማወቅ።

ጌታ የራሱ እንዲሆን ሰውን ሲጠራውና ተጠሪውም የፍቅር ግብዣውን ተቀብሎ ሕይወቱን ለአምላኩ ሲሰጥ ያ ሰው የእግዚአብሔር ይሆናል። በአዲስ ኪዳን (ሐዋርያው ጳውሎስ) "በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" ይላልና (1ቆሮ. 6:20) እግዚአብሔር ሰውን የራሱ ሲያደርግ፣ የሚከተሉት ነገሮች በአማኙ ሕይወት ውስጥ ይፈጸማሉ:-

- በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ይወለዳል። (ዮሐ. 3:5-9)
- የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ይሰጠዋል። (ዮሐ. 1:12)
- ከሞት ወደ ሕይወት ይሻገራል። (ዮሐ. 5:24)
- ከጨለማ ሥልጣን ይድናል። (ቆላ. 1:13)
- ወደ ክርስቶስ መንግሥት ይገባል። (ቆላ. 1:14)
- በክርስቶስ ደም ከኃጢአቱ ይነፃል። (1ዮሐ. 1:176 ኤፌ. 1:7)
- በመንፈስ ቅዱስ ይታተማል። (ኤፌ. 1:13)
- በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስና ያለ ነውር ይሆናል። (ኤፌ. 1:4)
- በክርስቶስ ኢየሱስ ሰማያዊ ዜጋ ይሆናል። (ኤፌ. 1:16 ፊል. 3:20)
- ስሙ በሕይወት መዝገብ ይጻፋል። (ራእይ. 20:15)
- የልብ ግዝረትን ይቀበላል። (ፊል. 3:3)
- ወደ ክርስቶስ አካል ይጠመቃል። (1ኛ ቆሮ. 12:13)
- መንፈሳዊ ትንሣኤን ያገኛል። (ቆላ. 2:12)
- ከኩነኔ ነፃ ይሆናል። (ሮሜ. 8:1)
- ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ይቀመጣል። (ኤፌ. 2:6)
- በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ይባረካል። (ኤፌ. 1:3)
- ብርሃን ይሆናል። (ኤፌ. 5:8፣ ማቴ. 5:14)

. ወዘተ

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ነገሮች በሕይወታችን ይሆናሉ። ስለዚህ እማኝን ለአገልግሎት የሚያበቁት ችሎታዎቹ ሳይሆኑ እነዚህ እግዚአብሔር በሕይወቱ የሚፈጽማቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህ አማኝ በመሪነትም ሆነ በሌላው አገልግሎት ውስጥ ከመግባቱ በፊት ከጌታ ጋር መሆኑን ማወቁ ከከንቱ ልፋትና ድካም ያድነዋል። ማንነቱን የማያውቅ አማኝ ደግሞ ለአገልግሎት አይበቃም። አገልግሎቱም ፍሬያማ አይሆንም። እንዲህ ብሏልና:- "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፤ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።" (ዮሐ. 15:5)



### 3ኛ የአገልግሎትን ኃላፊነት ማወቅ።

ስጦታንና ኃይልን በማደል ልጆቹን ለአገልግሎት የሚያሰማራ መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህም ስለሆነ መንፈስ ቅዱስ ከአገልግሎት ጋር ኃላፊነትን ይሰጣል። የአገልግሎት ኃላፊነትም ሁለት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ኃላፊነት ለሚጠራውና ለሚሾመው ጌታ ታማኝ መሆን ነው። ጌታ መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎት ሲጠራንና ሲሾመን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናገለግል መሆኑን እየገለጠ ጥሪያችንም ከሰው እንዳልሆነ ያስታውሰናል። "ለአክሪጳም በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ በሉልኝ።" "የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን ነውና።" (ቆላ. 4:17፣ 3:24) እንድናገለግል የምንጠራው እንደ ሎሌ ራሳችንን ዝቅ በማድረግና የሰዎችን እግሮች በማጠብ ብቻ ሳንወሰን መከራቸውንና ደስታቸውንም እንድንካፈል ነው። ለአገልግሎት ከመውጣት በፊት ከጌታ ሕይወት የአገልግሎትን ምስጢር መማርና አገልጋይነትን ከልብ መቀበል አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛው ኃላፊነት ደግሞ ጥሪው ሰዎችን ለማገልገል መሆኑን ማወቅ ነው። "ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን እንሰብክምና፣ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን።" (2ኛ ቆሮ. 4:5) እንግዲህ አገልግሎት እግዚአብሔርን ከማምለክ፣ በቃልና በኑሮ ጌታን ከማስከበር ጋር በፍቅር ለሌሎች አገልጋይና ሎሌ መሆን ነው። ሎሌነትም ኃላፊነትን የመቀበል እንጂ መብትን የማስከብር ጉዳይ እንዳልሆነ ሁሉ እኛም በክርስቶስ ፍቅር ራሳችንን ለሌሎች ባሮች አድርገን ስንሰጥ የምንወጣው ኃላፊነት እንጂ የምንከታተለው መብት የለንም። ጌታ ኢየሱስ ለመብቱ ለመቆም ቢፈልግ ኖሮ ስለ ኃጢአታችን ባልሞተም ነበር።

## ለውይይት የሚጠቅሙ ጥያቄዎች

1. ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የእግዚአብሔር ጥሪ ምንድነው?

2. እግዚአብሔርን ማወቅና በእግዚአብሔር ውስጥ ማንነታችንን ማወቅ ለፍሬያማ አገልግሎት የሚጠቅመው እንዴት ነው?

3. ሁሉም ሰው መሪ ወይም ሰባኪ ወይም ዘማሪ ለመሆን ካልተጠራ ታዲያ "አማኝ ሁሉ አገልጋይ ነው" ስንል ምን ማለታችን ነው?

4. ለምንድነው ጌታ ከስጦታችን ወይም ከችሎታችን በላይ የልባችንን ጉዳይ የሚመለከተው?

5. ስለ አገልግሎት ከጌታ ጋር ልታስተካክላቸው የምትወዳቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? ዘርዝራቸው።



# ም ዕ ራ ፍ   ሁ ለ ት

## የመንፈሳዊ መሪ ጥሪ

መንፈሳውያን መሪዎች የሚጠሩትና የሚሾሙት በእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ነው። አጠራራቸውና የተጠሩበት የአገልግሎት ዓይነት ግን ሊለያይ ይችላል። የእግዚአብሔር ጥሪ ግን ግልጽና የማያሻማ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ተመልከት።

| | |
|---|---|
| --ከአባትህ ቤት ...ተለይተህ ውጣ | ለአብርሃም |
| --የሕዝቤን ጩኸት ሰምቻለሁና | ለሙሴ |
| --ለሕዝቤ የተሰፋይቱን ምድር ታወርሳቸው.. | ለኢያሱ |
| --ለሕዝቤ እረኛ ትሆን ዘንድ | ለዳዊት |
| --ለእስራኤልም ቤት እንዲህ በል | ለነቢያት |
| --ሂድ ይህን ሕዝብ እንዲህ በል | ለኢሳያስ |
| --ብላቴና ነኝ አትበል | ለኤርምያስ |
| --የምወደው ልጄ ይህ ነው | ለጌታ ኢየሱስ |
| --ከእግዚአብሔር የተላከ | ለዮሐንስ |
| --ከኋላዬ ተከተሉኝ | ለደቀመዛሙርት |
| --ስሜን በአሕዛብና በነገሥታት ፊት | ለጳውሎስ |

እግዚአብሔር ሁሉንም በስርዓትና በቅደም ተከተል አቅዶ የሚሠራ አስደናቂ አምላክ ነው። ሥራው ሁሉ ዕቅድ ያለው ብቻ ሳይሆን ግብና ዓላማም ያለው ነው። የእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ ውበት ያለውና ውጤቱም ሁሉ የሚያረካ ነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚጀምረው ከመጀመሪያው ሲሆን የጀመረውንም ሥራ ሁሉ ደግሞ ከፍጻሜ ያደርሰዋል። ለምሳሌ ያህል ስለ ፍጥረት ብንጠቅስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቀን ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ከዚያ በኋላ በየቀኑ ለስድስት ቀናት በቅደም ተከተል ፍጥረትን ሁሉ

ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን አረፈ። ከዚህም ማስተዋል ከሚያስፈልጉን ነገሮች መካከል:-

ሀ) እግዚአብሔር ሁሉንም የፈጠረው በቅደም ተከተል ነበር፤

ለ) የፈጠረውን ሁሉ አንድ በአንድ ገመገመው "እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ፤" (ዘፍ. 1:10)

ሐ) ሰውን ከፍጥረት ሁሉ ለየት አድርጎ ፈጠረው፤

መ) ሰው ረዳት ያስፈልገዋል ብሎ እንደእርሱ የሆነችውን ረዳት ሰጠው፤

ሠ) ሰውን በሁሉም ነገር ላይ የበላይ ከማድረጉም ሌላ በራሱ መልክና እምሳል ስለ ፈጠረው እንደ አምላኩ የመኖርና የመሥራትን ጸጋና ኃላፊነት ሰጠው።

ሌላው ጥሩ ምሳሌ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ነው። ጌታ ኢየሱስ የዘላለም አምላክ ሲሆን ሥጋ በለበሰ ጊዜ ከመጀመሪያ ማለትም ከማኅፀን መጀመር ነበረበት። የተፈጥሮን ሕግ ተከትሎ ዘጠኝ ወር በማርያም ማኅፀን ውስጥ ከተቀመጠ በኋላ እንደ ሕፃን ተወልዶ ማደግ ነበረበት። "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ።" (ሉቃ. 2:52) ወላጆቹን በመታዘዝ በቤት ሆኖ ለሠላሳ ዓመት ያህል ካገለገላቸው በኋላ የጉባኤ አገልግሎቱን መስጠት ጀመረ። ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ሥራውን መፈጸሙን መስክሮ ወደ ክብሩ ተመለሰ። (ዮሐ. 17:4 ፣ ሉቃ. 24:51)

እነዚህ ነገሮች ከመሪ ጥሪ ጋር ምን ግንኙነት አላቸው? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። የእግዚአብሔር የተፈጥሮና የመንፈሳዊ አሠራሮች ለመሪ ጥሪ የአሠራር ዘይቤና ለሚጠበቀው ውጤት ቋሚ ምሳሌዎች ስለሆኑ እነዚህን በቅድሚያ መረዳት ለአመራር ሥራ የጠለቀ መሠረት ይሰጠዋል።

## የአገልግሎት ጥሪና የክርስቶስ ምሳሌነት

ስለ አገልግሎት ብዙ ጊዜ የሚጠየቀው ጥያቄ "መሪ ለአገልግሎት የሚጠራው መቼ ነው?" የሚል ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው



እግዚአብሔር በዕቅድና በሥርዓት የሚሠራ አምላክ ነው። የእቅድ አምላክ ስለሆነም በድንገት ወይም በአጋጣሚ አይሠራም። ለውጤት እንጂ ለታይታም ምንም ነገር አያደርግም። ለራሱ ክብር፣ ለሕዝቡ ጥቅምና በረከት የማይሆነውንም አይወጥንም። ሥራው ሁሉ ለአገልጋዩም ሆነ ለተገልጋዩ በረከት እንዲሆን የታቀደ ስለሆነ ዘላለማዊነት አለው። እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ዓለም ሳይፈጠር የጠራቸው ስለዚህ ነው። ይሁን እንጂ ጥሪው የተለያዩ ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው የሕይወት ጥሪ ነው። (ኤፌ. 1:4) ከአገልግሎት የሚቀድመው ነቀፋ የሌለበትን ሕይወት ከክርስቶስ በመቀበል የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ነው። ዘላለማዊና የተቀደሰ አገልግሎቱን ለመፈጸም እግዚአብሔር የሚጠቀመው የእርሱ በሆኑ ወይም በራሱ ደም አጥቦ በቀደሳቸው እግሮች ነው። ስለሆነም የመጀመሪያ ጥሪው ለሕይወትና ለልጅነት መሆኑን ማስተዋል ይጠቅማል። ሁለተኛው ጥሪ ደግሞ ሕይወትን ከተቀበልን በኋላ የእግዚአብሔር ጥሪ ለቅድስና ኑሮ ነው። "ዳሩ ግን:- እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።" (1ኛ ጴጥ. 1:15-16)

እንግዲህ እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነው አንደኛ በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረን ሲሆን ሁለተኛው የክርስቶስን ሕይወት እንድናንጸባርቅ ነው። ከነዚህ የሚከተል ሦስተኛው ጥሪው ለአገልግሎት መለየት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ከራሱ ጥሪ ጋር ሲያገናዝብ እንዲህ ይላል: "ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በፀጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርኩም።" (ገላ. 1:15-16) ሐዋርያ ጳውሎስ እግዚአብሔር ሦስት ነገሮችን በቅደም ተከተል በሕይወቱ እንደ ፈጸመ ይናገራል።

1ኛ. ከማኅጸን እንደለየው፣ ጥሪውም የድንገት ሥራ እንዳልነበረና ከዘለዓለም የታቀደ እንደ ሆነ ነው። ጌታ ኢየሱስ ስለራሱ ሲናገር "በዚያን ጊዜ እነሆ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ

አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ” ይላል። (ዕብ. 10:7)

2ኛ. በጸጋው እንደ ተጠራ፤ የእግዚአብሔር ጥሪ (ለሕይወትም ሆነ ለአገልግሎት) የምሕረቱ መግለጫ ነው እንጂ የተጠራውን ታላቅነት የሚያሳይ አይደለም። ስለዚህ ነው “በጸጋው ማረኝ” (1ኛ ጢሞ. 1:13–14) የሚለው። ጸጋ ሰው በራሱ መልካምነት ምክንያት ሊቀበለው የማይችለው፤ እግዚአብሔር በነጻ ሰውን የሚያለብሰው ሞገስ ነው። ይህ ሞገስ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት እንደ እግዚአብሔር ልጆችና አገልጋዮች እንድንቆም ድፍረትን ይሰጠናል። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተለየ መንፈሳዊ ድፍረት ወደ ታላቅ ውድቀት የሚመራ ሥጋዊ ትምክህት ነው። ከታላቁ ውድቀት ለመጠበቅ በሕይወትም ሆነ በአገልግሎት ውስጥ ራስን ከሥጋ ትምክህት መጠበቅ ከሁሉም መቅደም ያለበት ኃላፊነት ነው።

3ኛ. የእግዚአብሔር ጥሪ እንዴት መሆኑን፤ የክርስቶስ ሕይወት በአማኞች ሁሉ እንዲገለጥ የእግዚአብሔር ጥሪ አንድ ነው። ይህም ማለት ሕይወትን ከተቀበልን በኋላ የክርስቶስ ሕይወት በእኛ ሕይወት ውስጥ መታየት አለበት ማለት ነው። ስለዚህ የመሪ ጥሪ ሕይወቱ የክርስቶስን ክብር እንደ መስታወት እንዲያንጸባርቅ/ነው። “እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።” (2ኛ ቆሮ. 3:18)

የክርስቶስን ክብር ማንጸባረቅ ስንል እርሱ የአባቱን ባሕርይ እንዳንጸባረቀ እኛም የክርስቶስን ጠባይ በሁሉም ነገር ውስጥ ማሳየት ማለት ነው። “እርሱም የክብሩ መንፀባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።” (ዕብ. 1:3) ይህም የመሪውን አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ሕይወቱን ሁሉ የሚመለከት ነው። ክርስቶስ እንደ መሪ የአብን ባሕርይ እንዴት እንዳንጸባረቀ ለምሳሌ ያህል ብንመለከት የሚከተሉትን ነገሮች በግልጽ እናያለን።



ኛ➧ ሕይወቱ ያለነቀፋ ነበር። ስለዚህም መሪ በአኗኗሩ (በግልም ሆነ በጉባኤ) በቅድስና እንዲመላለስ ይጠበቅበታል።

2ኛ➧ የራሱን ዕቅድና ውጥን ይዞ ሳይሆን የአብን ፈቃድ ለመፈጸም ራሱን ሰጥቷል። “ፈቃድህን ለማድረግ መጣሁ።” ይላል። (ዕብ. 10:7) መሪም የክርስቶስን ክብር የሚያንጸባርቀው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሱን ሲያስገዛ ነው።

3ኛ➧ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተከትሏል። “ስለ እኔ እንደ ተጻፈ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ” ይላል። (ዕብ. 10:7) ክርስቶስ ከተጻፈው ውጭ ምንም ነገር አላደረገም። የአባቱን ዕቅድ በቅደም ተከተል ፈጸመ። የክርስቶስንም ክብር ለማንጸባረቅ የተጠራ መሪም እግዚአብሔርን መታዘዝ ብቻ ሳይሆን የሥራውንም ቅደም ተከተል ከእግዚአብሔር መቀበል አለበት።

4ኛ➧ ሥራውን ሁሉ አብ በወሰነው ጊዜ ሠርቷል። ይህንንም በየወቅቱ መስክሯል፤ ገልጿል። “ጊዜው በደረሰ ጊዜ…” (ገላ. 4:2)፣ “ጊዜዬ ገና አልደረሰም…።” (ዮሐ. 2:4፣7:6) መንፈስ ቅዱስ በውስጡ እየሠራ የጌታን ክብር ማንጸባረቅ የሚፈልግ አገልጋይም ሁሉ በራሱ ጊዜ ሳይሆን እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ መሥራትን መለማመድ ይኖርበታል። መሪ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን ጊዜውም የጌታ መሆኑን አጥብቆ መረዳትና በፈተና ጊዜ ይህንን ማስታወስ በጣም ይጠቅመዋል።

5ኛ➧ ያለገደብ ታዟል። “በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።” (ፊል. 2:5–8) በዚህ ጥቅስ ውስጥ ክርስቶስ አብን እንዴት እንደ ታዘዘ ማየት

እንችላለን:-

ሀ. መብቱን በመተው። መብቱን ለጌታ ያላስገዛ መሪ ለሥጋ ፈቃድ ስላልሞተ የክርስቶስን ክብር ማንጸባረቅ ያስቸግረዋል። ለሥጋው ፈቃድ በመሞት ለጌታ የሚኖር መሪ ግን በድፍረት:- "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።" ማለት ይችላል። (ገላ. 2:20)

ለ. ራሱን ዝቅ በማድረግ። እግዚአብሔርን ከፍ ለማድረግና ክብሩን ለሕዝብ ለማንጸባረቅ የተጠራ መሪም ራሱን ዝቅ ማድረግ አለበት። መሪነት የሚጀመረው በዙፋን ላይ ሳይሆን በጉልበት ላይ ነው። የእሾህ አክሊል የክብር አክሊልን ይቀድማል። ለእሾህ አክሊል ራሱን ያልሰጠ መሪ የክብር አክሊል ሊደፋ ብቁ አይሆንም። ብዙ ጊዜ ከተራራ በፊት ሸለቆ አለ። ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ "እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፣ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን" ያለው። (ሉቃ. 22:26) ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለዚህ ሲጽፍ "እንግዲህ በጊዜው ከፍ /እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ።" ይላል። (1ጴጥ.5:6)

ሐ. ለመስቀል ሞት በመታዘዝ። ክርስቶስ ያለገደብ አብን ታዟል። የራሱን ፈቃድ ትቶ የአብን ፈቃድ አደረገ። "ነገር ግን እንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።" (ማቴ. 26:39) ለሕዝቡ ሲል መራራ ጽዋ ጠጣ። ለሕዝቡ ከመሞቱ በፊት ለራሱ ፈቃድ ሞተ (ዮሐ. 12)።

ክርስቶስን ለማንጸባረቅ የሚፈልግ መሪ ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን አለበት። በሙሉ ልቡና በፍቅር "ክርስቶስ ከከበረ ይበቃኛል" ለማለት የማይችል ክርስቲያን የጌታን ክብር ማንጸባረቅ አይችልም።

6ኛ➧ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አገልግሏል። "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን



ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ ልኮኛል።" (ሉቃ. 4:18) የመሪ ጥሪ ለመለኮታዊ አገልግሎት ነው። መለኮታዊ ሥራ የሚሠራው በመለኮታዊ ኃይል ብቻ ነው ። ስለዚህ አንድ መሪ የጌታን ክብር ለማንጸባረቅ የሚችለው ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ራሱን እያስረከበ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ኃይል የሚሠራ ከሆነ ነው። ይህ ለማንኛውም አገልግሎት ቁልፍ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ ቅባት፣ ጸጋ፣ ስጦታና ፍሬ መሪ ሆኖ ለሌሎች የምሥራችን ማቅረብ የማይቻል ነገር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢዩ:- "በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" (ዘካ. 4:6) ሲል የተናገረው። ኢየሱስም ለሐዋርያት "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ:- በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።" ብሏል። (የሐዋ. 1:8)

7ኛ➧ በጸሎት ከአብ ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት አድርጓል። "ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፣ ..." (ሉቃ. 3:21)፤ "በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ አደረ።" (ሉቃ. 6:12፣ ማቴ. 14:23፣ ማር. 1:35...ወዘተ)። የእግዚአብሔርን ክብር ለማንጸባረቅ መሪ ባለማቋረጥ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት አለበት። ሙሴ በተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሮ ሲመለስ ፊቱ የእግዚአብሔርን ክብር አንጸባረቀ። በሕዝቡ መካከል የተቀመጠው አሮን ግን የሕዝቡን ውዳሴ ለማግኘት የወርቅን ጣዖት ሠራላቸው። የሚጸልይ መሪ የጌታን ክብር ያንጸባርቃል፣ ጣዖታትንም ከሕዝቡ መካከል ያስወግዳል።

8ኛ➧ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ በመናገር የአባቱን ባሕርይ ገልጿል። በእውነተኞችና በሐሰተኞች ነቢያት መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት ሐሳውያን ከእግዚአብሔር የሰሙትን ብቻ በመናገር ፈንታ ከራሳቸው የሚፈጥሩትን መናገራቸው ነበር። እግዚአብሔርን የሚያስከብር መሪ ከራሱ አይናገርም፤

እግዚአብሔር በተናገረው ላይ አይጨምርም፣ የተነገረውንም በፍቅር ከመናገር ወደ ኋላ አይልም።

9ኛ፦ የአብን ሥራ ብቻ ሠርቷል። "አባቴ ሲሠራ ያየሁትን..." የጌታን ክብር የሚያንጸባርቅ አገልጋይ የሥጋን ሥራ አይሠራም። ስለሚያመችና ስለማያመች አይሠራም። ተቀባይነት ስላለውና ስለሌለው አያገለግልም። የእግዚአብሔር ዕቅድና ፈቃድ ስለሆነ ብቻ በደስታ ያገለግላል።

10ኛ፦ ጥሪውና አገልግሎቱም በአብ ተመስክሮለታል። ክርስቶስ የአብን ባሕርይ ገልጧል። እግዚአብሔር አብም ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽና በጉባኤ መካከል ሦስት ጊዜ በመመስከሩ ከእርሱ መላኩን አረጋገጠ። አንደኛ <u>ጥሪው</u> <u>ከእርሱ መሆኑን አጸደቀ</u>። "ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሀ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በርሱ ላይም ሲመጣ ታየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።" (ማቴ. 3:16–17) የክርስቶስ ጥሪ ከእርሱ ዘንድ መሆኑን እግዚአብሔር አብ በሦስት መንገዶች አጽድቋል/ወይም አረጋግጧል።

ሀ. መንፈስ ቅዱስ በአካል መልክ እንዲወርድበት በማድረግ። ጌታ ኢየሱስም አገልግሎቱን ሲጀምር "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው" (ሉቃ. 4:18) ያለው፣ ይህ ዓይነት ምስክርነት ስለ ነበረው ነው። የኩራትና ራሱን የማመጻደቅ ሳይሆን ይህ የእግዚአብሔር ተልእኮ መሆኑንና በእርሱ ኃይልና ለእርሱ ክብር ብቻ የሚሠራ እንደሆነ ለማረጋገጥ ነው።

ለ. ከእግዚአብሔር ዘንድ በመጣው የምስክር ቃል "የምወደው ልጄ ይህ ነው።" (ማቴ. 3:17) በማለት ይህ ሰው የእኔ ነው። ይህ ሰው ከእኔ ነው። ይህ ሰው ለእኔ ክብር ነው አለ። ከአገልግሎቱ በፊት እግዚአብሔር የሚቀበለው ሰውን ነው ። እግዚአብሔር ስለ ጌታ ሲናገር "የምወደው ልጄ" አለ እንጂ "የምወደው አገልግሎቴ" አላለም። እግዚአብሔር ስለ አገልግሎታችን ከመመስከሩ በፊት ስለ ሕይወታችን የሚመሰክረው በጣም ይበልጣል። ዋጋው ከክብር ዕንቁ ይበልጥ ታላቅና



ክቡር ነው። እግዚአብሔር አንድ ነገር "የእኔ" ነው በሚልበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ፈቃዱ ይገለጽበታል፤ ክብሩ ይታይበታል፤ ዓላማውም ይከናወንበታል ማለት ነው። አገልግሎታችንን ከመጀመራችን በፊት በእግዚአብሔር መንፈስ ሙላትና ቁጥጥር ሥር መሆናችን በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ስለ መሪ አገልግሎት ከመናገሩ በፊት ስለ ሕይወቱ ካልመሰከረ አገልግሎቱ ዋጋ የለውም። አስፈላጊውና መቅደም ያለበት ጥያቄ "እግዚአብሔር ስለ አገልግሎቴ ምን ይላል?" ሳይሆን "ስለ ሕይወቴ ምን ይላል?" የሚል መሆን አለበት። እግዚአብሔር ስለ ግልና ስለ ጉባኤ ሕይወቱ የሚመሰክርለት አገልጋይ ብጹዕ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል መሰከሯል "እርሱም ገና ሲናገር እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው እነሆም ከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።" (ማቴ 17:5) የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያው ክፍል ከማቴዎስ 3:17 ጋር አንድ ነው። ስለ ክርስቶስ ሕይወት በአገልግሎቱ መካከል የተሰጠ ምስክርነት ነው። እግዚአብሔር ስለ አገልጋይ ሕይወት የሚመሰክረው አገልግሎቱን ሲጀምር ብቻ አይደለም በአገልግሎቱም መካከል ይመሰክርለታል። ሌላው ትልቁ ቁም ነገር ምስክርነቱ አንድ ዓይነት መሆኑ ነው። ስለ እኔና ስለአንተ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት የመሰከረውን ዛሬም ደፍሮ ሊመሰክርልን ይችል ይሆንን? በሁለተኛው (ማቴ. 17:5) ምስክርነቱ ላይ የተጨመረ አረፍተ ነገር "እርሱን ስሙት" የሚል ነው። ይህ የአገልግሎት ሥልጣን ነው። እውነተኛና ዘለቄታ ያለውን ፍሬ የሚያስገኝ አገልግሎት እግዚአብሔር ስለ ጅምሩ ሲመሰክርና የአገልግሎቱ ሥልጣን ከእርሱ ሲመጣ ብቻ ነው። እግዚአብሔር "እርሱን ስሙት" በሚልበት ጊዜ የክርስቶስን ሥልጣን ማጽደቁ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ የሚናገረው የአብን ድምጽ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጡ ነው። "እርሱን ስሙት" የእኔ ድምጽ ነው። የእኔ መልእክት ነው ማለቱ ነው። የክርስቶስ ሥልጣን ከላይ መሆኑን እግዚአብሔር አብ በመመስከር አጸና። ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስና ያዕቆብ ክብሩን አዩ ምስክሩንም ሰሙ። የእግዚአብሔር ክብር በሕይወቱ ተገለጠ፤ የእግዚአብሔርም ሥራ በእጁ

## ለውይይት የሚረዱ ጥያቄዎች

1▶ እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በቅደም ተከተልና በሥርዓት መሥራቱን መረዳት ለአንድ መሪ እንዴት ይጠቅመዋል?

2▶ እግዚአብሔር ሰውን የሚጠራው ለምንድነው?

3▶ የአገልግሎት ጥሪ ከሕይወት ሊቀድም አይችልም። ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው?

4▶ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥሪ፣ ስለ መሪ ጥሪና ሕይወት ምን እንማራለን?

5▶ በመሪነት አገልግሎት ውስጥ የእግዚአብሔር ምስክርነት አስፈላጊነቱ ለምንድነው?



## ም ዕ ራ ፍ ሦ ስ ት

## መሪዎች የሚጠሩት በማን ነው ?

በአካባቢያችን በምንመለከትበት ጊዜ የተለያዩ መሪዎች እንዳሉና እነርሱም ወደመሪነት ለመምጣት የተለያዩ ምክንያቶች፣ ፍላጎቶችና ዓላማዎች እንዳሏቸው ማየት አያስቸግርም። ለምሳሌ ያህል ብጠቅስ:-

1ኛ▶ ራሳቸውን የሚሾሙና ጥሪያቸውን ለማጽደቅ ደጋፊዎች የሚፈልጉ መሪዎች አሉ።

2ኛ▶ በሰዎች የሚሾሙና ያንን ተቀብለው በመሪነት አገልግሎት ውስጥ የሚገቡም አሉ። ብዙ ጊዜ ይህ የሚሆነው ሰውየው የተፈጥሮ ችሎታ ስላለው ወይም ኃላፊነቱን የሚቀበል ሰው ስለሚጠፋ “ግድ የለም፣ ለጊዜው እርሱ ይሁን” ይባልና መሪ ይሆናል። ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ለቦታው (ሁነኛ) ጥሪ ያለው ሰው ሲመጣ ቦታውን መልቀቁ (ሥልጣን ስለሚጥም) በጣም ችግር ይሆናል።

3ኛ▶ ሥልጣን ስለሚወዱ በማናቸውም ዓይነት መንገድ ይሁን የመሪነትን ደረጃ የሚይዙም አሉ።

4ኛ▶ ሥልጣን ስለሚሰጠው ጥቅም ሲሉ መሪ የሚሆኑም ብዙዎች ናቸው። ጥቅሙ የገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ማዘዝንም ይጨምራል።

5ኛ▶ እግዚአብሔር ለአገልግሎት ጠርቷቸው ያንን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ሥጋ ፈቃድ በመዞር እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥልጣን በማይገባ ቦታ የሚያውሉም አሉ። እነዚህ በመንፈስ ጀምረው በሥጋ የሚጨርሱ እንደ ሳዖል ዓይነቶች ናቸው።

6ኛ▶ እግዚአብሔር ጠርቷቸው ሳለ የእርሱን ጊዜ ሳይጠብቁ ተቻኩለው በመሪነት ሥራ ውስጥ የሚገቡ አሉ። ሙሴ በመጀመሪያ በዚህ ስህተት ውስጥ ገብቶ ነበር። (ዘፀ. 2:12-15)

ፓኖ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምተው በእግዚአብሔር ጊዜና ፈቃድ በእግዚአብሔርም መንገድ በመሪነት ኃላፊነት ውስጥ የሚገቡ አሉ። ይህ ትክክለኛው ወደ አገልግሎት መግቢያ መንገድ ነው። እንግዲህ አንድን ሰው ለመሪነት የሚጠራ እግዚአብሔር ነው። ከእግዚአብሔር ካልተሰጠው በስተቀር ሰው መሪ ሆኖ እግዚአብሔርን ለማክበርና ለሌሎችም በረከት ለመሆን አይችልም። በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ መሪን የሚጠራና የሚሾም እግዚአብሔር ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በመሪነት የተጠሩትን (በተለይም ነገሥታትንና ካህናትን) ብንመለከት ጥሪያቸው ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማጽደቅ፣ በዘይት ቀብተው በሕዝብ ፊት የሚሾሙ ነቢያት ይላኩላቸው ነበር።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለመሪነትም ሆነ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ጠርቶ የሚሾም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ጥሪውን የሚያጸድቁት ክርስቲያኖች ናቸው። ለምሳሌ ያህል :- "እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ:- መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቷቸው።" (የሐዋ. 13:2-3) በርናባስንና ሳውልን ለአገልግሎት የጠራቸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ ጥሪውን/ በማጽደቅ እንዲልኩአቸው ሥልጣን የተሰጠው አብሮአቸው ለነበሩት ቅዱሳን ነበር።

እንግዲህ መሪን ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ የሚለይ እግዚአብሔር ነው። ጊዜው ሲደርስ ጥሪውን ወደዚያ ሰው የሚልከውም እግዚአብሔር ሲሆን ጥሪው ከእርሱ መሆኑን የሚያስጸድቀው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ወይም በቅዱሳን ሕብረት ነው። የግለሰቡን ሕይወት ለአገልግሎት ያዘጋጀው እግዚአብሔር ይህንን ጥሪ እንዲያጸድቁ የምእመናንን ልብ በሰላም ይሞላል።

እግዚአብሔር በጠራቸውና ራሳቸውን በራሳቸው በሾሙት መሐከል ብዙ ልዩነት አለ። እነዚህን ልዩነቶች መረዳት ቤተ ክርስቲያንን በሚከተሉት መንገዶች ይጠቅሙዋታል:-

ሀ) ከእግዚአብሔር ተልከው ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡትን አገልጋዮች ቤተክርስቲያን በሥጋ አመለካከት አይታ እንዳትቃወም ይረዳታል።



ለ) እግዚአብሔር የቀባቸውንና የሾማቸውን መሪዎች በአክብሮት ተቀብላ እንድትታዘዝ ያስችላታል። እግዚአብሔር የቀባቸውን መታዘዝ ለግለ ሰብም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ በረከት ነው። ይህ ሲሆን የምናከብረው አገልጋዮቹን ብቻ ሳይሆን በእነርሱ ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቅባት ነው። ንጉሡ ዳዊት ለዚህ መልካም ምሳሌ ነበር። ሊገድለው የሚያሳድደውን ሳዖልን እንዲበቀል ወታደሮቹ በመከሩት ጊዜ እርሱ ግን:- "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን አላነሳም" አለ። እግዚአብሔርም ዳዊትን ጠብቀው፣ ባረከው፣ ዙፋኑንም አጸናለት። የክርስቶስ ኢየሱስም ዘር ለመባል በቃ።

እርሱ የቀባቸውንና የሾማቸውን ሰዎች እንድናከብራቸው የጌታ ቃልም በግልጽ ያስተምረናል። "በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፣ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።" ይላል። (1ኛ ጢሞ. 5:17) ከዚህም በላይ ከጌታ የተሰጠውን ሥልጣን መናቅ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ መሆን እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተጽፎአል። (ይሁዳ 1:8-12)

ሐ) ከእግዚአብሔር የተላኩትን ጠንቅቃ ማወቁ ሐሰተኞችን ከእውነተኞቹ ለይታ ለማወቅ ይጠቅማታል። ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተላኩትን መቀበል ብቻ ሳይሆን ሳይላኩ ተልከናል የሚሉትንም መለየትና ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ማስወገድም ግዴታዋና ኃላፊነቷ ነው። "ሥራህንና ድካምህን ትዕግስትህንም አውቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገስ እንዳትችል፣ እንዲሁም ሳይሆኑ ሐዋርያ ነን የሚሉትን መርምረህ ሃሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፤" (ራእ. 2:2) "ዳሩ ግን:- ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤" (ራእ. 2:20)

## በእግዚአብሔር በተጠሩትና ባልተጠሩት መሐከል ያለው ልዩነት

የሚከተሉት ነጥቦች እግዚአብሔር የጠራቸውንና የሾማቸውን ሰዎች፣ ራሳቸውን ከጠሩትና ከሾሙት ሰዎች ለይቶ ለማወቅ በመጠኑም ቢሆን ይረዳ

| በእግዚአብሔር የተጠሩ | በሥጋ የተጠሩ |
|---|---|
| 1. በእግዚአብሔር ብቻ ይታመናሉ | .በራሳቸው ብዙ ይታመናሉ |
| 2. ከጌታ የመጣውን ጥሪ በፍርሃት በአክብሮት ይቀበላሉ | .ሹመታቸው የመጣው ከሰዎች ነው |
| 3. በእግዚአብሔርና በቅዱሳን ጥሪና ፀሎት ተሹመዋል | .በራሳቸው ወይም በሰዎች ተሹመዋል |
| 4. ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ያስገዛሉ | .ምኞታቸውን ለመፈጸም ይተጋሉ |
| 5. ዓላማቸው ለማገልገል ነው | .ዓላማቸው ለመዛት ነው |
| 6. በትሕትና ያገለግላሉ | .በኩራት ይመካሉ |
| 7. በእግዚአብሔር ላይ ይታመናሉ | .በችሎታቸው ይታበያሉ |
| 8. የጌታ ራእይ አላቸው | .በሥጋ ምኞት ይመራሉ |
| 9. በጌታ ጸጋና ቸርነት ይመካሉ | .በውጫዊ ሥርዓት ይመካሉ |
| 10. በጌታ ቃል ይመራሉ | .የጌታን ቃል ለሥጋ እንደሚመች ይለውጡታል |
| 11. የመንፈስ ኃይልና ፍሬ በሕይወታቸው ይታያል | .ስለ ስጦታቸው ብቻ ይናገራሉ ግን የመንፈስ ፍሬ አይታይባቸውም |
| 12. የልባቸው ሸክም የጌታ ሥራ ነው | .የራሳቸውን ምቾት መጠበቅን ያስቀድማሉ |



| | |
|---|---|
| 13. ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ | .ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጋሉ |
| 14. የታዛዥነት መንፈስ አላቸው | .ማዘዝ እንጂ መታዘዝ አይወዱም |
| 15. ሁሉንም እኩል ያያሉ | .አድልዎ ይታይባቸዋል |
| 16. ለውለታ ብለው አይሠሩም | .ከሰው ብድራትን ለማግኘት ይወዳሉ |
| 17. በሙሉ ልባቸው ያገለግላሉ | .ቸልተኝነት ያጠቃቸዋል |
| 18. ዓላማና ግብ አላቸው | .እንደ ሁኔታው ሃሳባቸውን ይቀያይራሉ |
| 19. ለራሳቸውና ለአገልግሎቱ ይጠነቀቃሉ | .ጥንቃቄ ይጎላቸዋል |
| 20. ስለ ሁሉም ጌታን ያመሰግናሉ | .ራሳቸውን ያሞግሳሉ |
| 21. ብርታታቸውንና ድካማቸውን ያውቃሉ | .በብርታታቸው ይመካሉ ድካማቸው አይታያቸውም ወይም ይደብቃሉ |
| 22. ምስጋና ይበዛላቸዋል | .ማጉረምረምን ያበዛሉ |
| 23. ለጥሪውና ለሕዝቡ ታማኞች ናቸው | .ታማኝነታቸው ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ነው |
| 24. በአገልግሎታቸው ደስተኞች ናቸው | .ብዙ ደስታ አይታይባቸውም |
| 25. የቅዱሳንን ልብ ደስ ያሰኛሉ | .የቅዱሳንን ልብ ያሳዝናሉ |
| 26. በቀላሉ ተስፋ አይቆርጡም | .በትንሹ ተስፋ ይቆርጣሉ |
| 27. ሌሎችን ያጽናናሉ በሌሎችም ይጽናናሉ | .ብዙም አይሰጡም እንዲሁም አይቀበሉም |
| 28. ሌሎችን ያዳምጣሉ | .ይናገራሉ እንጂ አያዳምጡም |

| | |
|---|---|
| 29. ምክርን ይቀበላሉ | .ምክር መቀበል ይከብዳቸዋል |
| 30. ራእያቸው ሰማያዊ ነው | .ራእያቸው ሥጋዊና ምድራዊ ነው |
| 31. ራእያቸው ግልጽ ነው | .ራእያቸው ግለጽ አይደለም |
| 32. የመንፈስን ነገር ያስቀድማሉ | .ለሥጋ ፈቃድ ቅድሚያ ይሰጣሉ |
| 33. አንድነትን ይፈጥራሉ | .አንድነትን ያፈርሳሉ |
| 34. እግዚአብሔርን ያዳምጣሉ | .ሰዎች ስለእነርሱ የሚሉትን ለመስማት ቅድሚያ ይሰጣሉ |
| 35. ለታይታ ብለው አያገለግሉም | .ሁሉም እንዲታወቅላቸው ይፈልጋሉ |
| 36. ጸሎትን ያስቀድማሉ | .የጸሎት ሕይወታቸው ውስን ነው |
| 37. የይቅርታ ልቡና አላቸው | .ቂም መያዝን ያበዛሉ |
| 38. የጌታን ሥራ ሰፋ አድርገው ያያሉ | .የጌታን ሥራ በራሳቸው ልምምድና አመቺነት ይወስናሉ |
| 39. በሌሎች አገልግሎትና ስጦታ ያምናሉ | .የሌላውን አገልግሎት እንደሚገባ አያከብሩም |
| 40. የጌታን ጊዜ ይጠብቃሉ | .በራሳቸው ጊዜ ይሠራሉ |
| 41. በጌታ መንገድ ይሠራሉ | .በራሳቸው ዘዴ ይጠቀማሉ |
| 42. በሥልጣን ሕዝቡን ያገለግላሉ | .ሥልጣንን ለመገልገል ይጠቀሙበታል |
| 43. ምእመንን ለመጥቀም ይጥራሉ | .የራሳቸውን ጥቅም ያስቀድማሉ |
| 44. በፍቅር ራሳቸውን መስዋዕት ያደርጋሉ | .ብዙ ጊዜ ያደረጉትን ይቆጥራሉ |
| 45. የጌታን መንግሥት ለማስፋት | .የራሳቸውን የሥልጣን ድንበር |



| | |
|---|---|
| ይተጋሉ | ለማስፋት ይጥራሉ |
| 46. ዓላማቸው ጌታን ማስደሰት ነው | .ራሳቸውን ለማርካት ነው |
| 47. በቃሉ መሠረት ያገለግላሉ | .በፈቃዳቸው መሠረት ያገለግላሉ |
| 48. ምሥጋና ለሚገባው ምስጋና ይሰጣሉ | .ማመስገንን ሳይሆን መመስገንን ይሻሉ |
| 49. የሌሎችን ሕይወት ይገነባሉ | .ለሌሎች የሚገባ ጥንቃቄ አያደርጉም |
| 50. ሕዝብን በሕይወት ምሳሌነትና በእምነት ይመራሉ | .ሕዝብን በሕይወት ምሳሌነት ከመምራት ይልቅ ያስጨንቋቸዋል |

በታሪክ ውስጥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በረከት የሆነና ዘለቄታ ያለውን ነገር ሠርተው ያለፉት መሪዎች በሰዎች የተጠሩና ወይም ራሳቸውን የሾሙ አይደሉም። በእግዚአብሔር የተዘጋጁና የተጠሩ ብቻ ነበሩ። ለምሳሌ ያህል ብንመለከት ሙሴ የተጠራው በእግዚአብሔር ነበር። "እግዚአብሔርም እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ፦ ሙሴ፣ ሙሴ ሆይ አለ።" (ዘፀ.3:4) እግዚአብሔር ስለጠራው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነፃ ሊያወጣ ቻለ። እግዚአብሔርንም እንዲያመልኩ ሥርዓትን ተቀበለ። ሕዝቡም በሙሴ አማካኝነት የእግዚአብሔርን ምሕረትና ምሪት አዩ።

ሌላው በእግዚአብሔር የተጠራው ዳዊት ነበር። ዳዊት ከእረኛነት ተፈልጎ በእግዚአብሔር ተሾመ። ለሕዝቡም ንጉሥ ብቻ ሳይሆን እረኛ ሆነላቸው። በመዝሙር፣ በውዳሴና በቅኔ ሰዎች አምላካቸውን እንዲያመልኩና በተስፋም እንዲሞሉ አደረገ።

ሳሙኤልም በእግዚአብሔር የተጠራ መሪ ነበር። "እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ እንደ ቀድሞውም ሳሙኤል ሳሙኤል ብሎ ጠራው። ሳሙኤልም ባርያህ ይሰማልና ተናገር አለ።" (1ኛ ሳሙ.3:10) መገለጥን

ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለሕዝቡ እንደ ነቢይና እንደ እውነተኛ ዳኛ አገለገላቸው። እንደ እግዚአብሔርም ቃል ደንብን መሠረተላቸው። እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነውን ንጉሥ ቀባላቸው።

ጳውሎስም ከአሳዳጅነት ለሐዋርያነት በጌታ ተጠራ። የሐዋርያነት አገልግሎቱንም በታማኝነት ፈጸመ። ከጌታ የተቀበለውን ቃል ለቤተ ክርስቲያን ምንም ሳይጨምርበትና ሳያጎድል አስተላለፈ። መንፈስ ቅዱስ መንገድህን ቀይር ባለው ጊዜ ታዘዘ። ኃይማኖቱን ጠበቀ፤ ሩጫውንም ጨረሰ። ይህም በእግዚአብሔር የመጠራት ምልክት ነው።

እንግዲህ በእግዚአብሔር የተጠሩት መሪዎች ዋና ምልክታቸው እንደሚከተለው ነው:-

- የእግዚአብሔርን ዓላማ ይፈጽማሉ፤
- ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ያቀርባሉ፤
- የእግዚአብሔርን ሥራ ለሕዝብ ያሳያሉ፤
- ሰዎችን ወደ እምልኮ ይጠራሉ፤
- በእግዚአብሔርም ተስፋ ይሞሉዋቸዋል፤
- ለጌታ ሥራና አገልግሎት የወደፊት መሪዎችን ያዘጋጃሉ።

እነዚህን ኃላፊነቶች ለማከናወን ያስቻላቸው እግዚአብሔር ሲጠራቸው ያዩትና የሰሙት፤ በሕይወታቸውም የተለማመዱት መለኮታዊ ምሥጢር ነው። እግዚአብሔር መሪን ሲጠራ፤ በመሪም ሕይወት ውስጥ ስለሚሆኑ ነገሮች በግል ሕይወቱ የሆነውን ሲመሰክር ሐዋርያው ጳውሎስ ሐናንያ ያለውን በመጥቀስ እንዲህ ይላል:- " እርሱም አለኝ:- የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጻድቁን ታይ ዘንድ ከአፉ ድምጽን ትሰማ ዘንድ አስቀድሞ መርጦሃል ባየኸውና በሰማኸው በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆናለህና።" (የሐዋ. 22:14-15)

እላይ በተጠቀሰው ጥቅስ መሠረት እግዚአብሔር ለሚጠራቸው መሪዎች ሁሉ ያለው ዓላማ እንደሚከተለው ነው:-

1ኛ▸ የእርሱን ፈቃድ እንዲያውቁ። "ፈቃዱን ታውቅ ዘንድ፤" እግዚአብሔር የጠራው መሪ ፈቃዱን ያውቃል፤ ያደርጋልም።

2ኛ▸ እርሱን እንዲያዩ። "ጻድቁን ታይ ዘንድ፤" የመንፈሳዊ መሪ



ጥሪው ክርስቶስን ማየትና ማሳየት ነው። ጳውሎስ "ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፤" ይላል። (ገላ. 1:16)

3ኛ▸ እርሱን እንዲሰሙ። "ከአፉም ድምጽን ትሰማ ዘንድ"፤ እግዚአብሔርን የማይሰማ አገልጋይ መንፈሳዊ መሪ ሊሆን አይችልም። ከራሱ የማይናገር ከሆነ ከላይ የመጣውን መስማት ግዴታ አለበትና።

4ኛ▸ ምስክሮች እንዲሆኑ። "ባየኸውና በሰማኸው በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆንለታለህ።" በእግዚአብሔር የተጠራ መሪ እግዚአብሔር ሲያደርግ ያየውንና ሲናገር የሰማውን በሰው ፊት ሳያደላ ለሁሉም ያስተላልፋል።

እንግዲህ "መሪን የሚጠራው ማን ነው?" ለሚለው ጥያቄ አጠቃላይ መልሱ፤ መንፈሳዊውንና እውነተኛውን መሪ የሚጠራው እግዚአብሔር ነው። እርሱ መሪን ይጠራል፤ ይቀባል፤ ፈቃዱን ይገልጥለታል፤ ማንነቱን ያሳየዋል፤ ኃይሉን ይሰጠዋል፤ ድምጹን ያሰማዋል፤ ለሕዝቡም በረከት ያደርገዋል። የእግዚአብሔር ሰዎች ኃላፊነት ግን ከእግዚአብሔር በሆኑትና ባልሆኑት መካከል መለየትና ከእርሱ ለሆኑት መታዘዝ ነው። በመጨረሻም ምዕመኑ ከእግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡትን መንፈሳዊ መሪዎች በጸሎት፣ በገንዘብና በሌላም በሚያስፈልጉዋቸው ነገሮች ሁሉ የመደገፍና የመንከባከብ ኃላፊነቱን ተረድቶ መቀበል ይገባዋል።

ለመሪነት እግዚአብሔር ጠርቶናል ብለው ጥሪውን የተቀበሉት መሪዎች:-

- ሕይወታቸውን በቅድስናና በንጽህና መጠበቅ፤
- ለሚከተሉዋቸው ምሳሌ መሆን፤
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ ማወቅ፤
- የክርስቶስን ሕይወት ማንጸባረቅ፤
- ከእርሱ የሰሙትን ብቻ መናገር፤
- ሕዝቡን እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ መምራት፤
- ሌሎችን ለአገልግሎት በማዘጋጀት ጥሪአቸውን መፈጸም ይገባቸዋል።

## ለውይይት የሚጠቅሙ ጥያቄዎች

1) ሰዎች ወደ ሥልጣን የሚመጡት በምን መንገዶች ነው?

2) "መንፈሳዊ መሪን የሚጠራ ጌታ ነው" ስንል ምን ማለታችን ነው?

3) በአሁኑ ጊዜ አገልጋይን ለጥሪ መለየት የማን ኃላፊነት መሆን አለበት?

4) በጌታ የተጠሩትን እውነተኞች አገልጋዮች እንዴት ነው መለየት የምንችለው?

5) ጌታ ጠርቶናል ከሚሉ መሪዎች የሚጠበቁት አራት ነገሮች ምንድናቸው?



# ም ዕ ራ ፍ  አ ራ ት

## የ አ ገ ል ግ ሎ ት  ዝ ግ ጅ ት

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ተረጭተው በመንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ አካል በመጠመቅ የእርሱ ለሆኑት ሁሉ ዘላለማዊ የሆነ እቅድ አለው። የእግዚአብሔር እቅድ ለሁሉም እንደየድርሻው የተለያየ ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱን ለእያንዳንዱ ሰው በሚገባው መንገድ በጊዜው ግልጽ ያደርጋል። ይህም ስለሆነ የአገልግሎት ጅማሬ ለሚገለጸው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሙሉ ልብ መታዘዝ ነው። እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ መኖሩን ነው። "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና" (1ተሰሎ. 4:3)። ለዚህ ለተገለጸው የእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር (መታዘዝ) ለማንኛውም የአገልግሎት ጥሪ መሠረት ነው።

ቀዳሚው የቅዱሳን ጥሪ ለሕይወት ቅድስና ነውና። ቅዱሳንን በቅድስና ሕይወት ለማኖር እግዚአብሔር ጥሪውን ብቻ ሳይሆን ለዚህ የሚያበቃቸውንም ኃይል ለልጆቹ ሰጥቷል። "የመለኮቱ ኃይል፣ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፣ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፣ ... " (2ጴጥ. 1:2–3) እግዚአብሔርን በመምሰል በቅድስናና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መኖር ለእግዚአብሔር የክብር እቃ ለመሆን ያበቃል። "እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነጻ፣ ለክብር የሚሆን የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል።" (2ጢሞ. 2:21) የዕቃው ባለቤት ዕቃውን ካነጻ በኋላ እያንዳንዱን የቤት ዕቃ እንደ ተፈላጊነቱ ብርጭቆን ለመጠጫ፣ ሳህንን ለመብያ፣ ድስትን ለማብሰያ ወዘተ እንደሚያገለግል ሁሉ እግዚአብሔርም ለሥራው

